# BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## What time do you have breakfast?

## ቁ ር ስ የ ምት በ ላ ው ስ ን ት ሰ ዓ ት ላ ይ ነ ው?

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። በዛሬው ክፍል ስንት ሰዓት ላይ ቁርስ እንደሚበሉ 'have breakfast' እንዲሁም ስንት ሰዓት ላይ እራት እንደሚበሉ 'have dinner' መናገርን እና መጠየቅን ይማራሉ።
ሁለቱ ሰዎች ስለምግብ ሰዓቶቻቸው ሲያወሩ ያዳምጧቸው።

***Jane***
*Hi Chris, when do you have breakfast?*

***Chris***
*I never have breakfast.*

***Jane***
*When do you have dinner?*

***Chris***
*I have dinner at eight forty five.*

**ዘሩባቤል**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን። በመጀመሪያ ጄን ክሪስን ስንት ሰዓት ላይ ቁርስ እንደሚበላ 'have breakfast' ነው የጠየቀችው። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*When do you have breakfast?*

**ዘሩባቤል**
ክሪስ 'never' መቼም ቁርስ እንደማይበላ 'have breakfast' ነው የመለሰላት። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*I never have breakfast.*

**ዘሩባቤል**
ከዚያም ጄን ስንት ሰዓት ላይ ራት እንደሚበላ 'have dinner' ጠየቀችው። ስለጊዜ ጥያቄ ለማቅረብ 'when' እና 'what time' መጠቀም እንችላለን። የትርጉም ልዩነት የላቸውም። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*When do you have dinner?*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
ክሪስ ራቱን የሚበላው 'eight forty five' ለሶስት ሩብ ጉዳይ እንደሆነ ነገራት። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*I have dinner at eight forty five.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ምግቦችን ስንት ሰዓት ላይ እንደሚበሉ ሲነጋገሩ በማዳመጥ እርስዎ ካሉት ጋር ያመሳክሩ።
ኒክ ቁርስ የሚበላው ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ላይ ሲሆን 'lunch' ምሳ ደግሞ ስድስት ከሩብ ላይ ይበላል።

*Hi Nick, what time do you have breakfast?*

*I have breakfast at six forty five.*

*Ok. What time do you have lunch?*

*I have lunch at twelve fifteen.*

**ዘሩባቤል**
እሺ፤ አሁን ደግመን እንሞክር። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሮቹን ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያዳምጧቸዋል።

*When do you have breakfast?*
*When do you have breakfast?*

*I never have breakfast.*
*I never have breakfast.*

*I have breakfast at eight fifteen.*
*I have breakfast at eight fifteen.*

*When do you have dinner?*
*When do you have dinner?*

*I have dinner at eight forty five.*
*I have dinner at eight forty five.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንደሚያስታወሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*ቁርስ የምትበላው ስንት ሰዓት ላይ ነው*
*When do you have breakfast?*

*ቁርስ አልበላም*
*I never have breakfast.*


© British Broadcasting Corporation 2018

*ቁርስ የምበላው ሁለት ከሩብ ላይ ነው።*
*I have breakfast at eight fifteen.*

*እራት የምትበላው ስንት ሰዓት ላይ ነው?*
*When do you have dinner?*

*እራት የምበላው ለሶስት ሩብ ጉዳይ ላይ ነው።*
*I have dinner at eight forty five.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ግሩም፤ አሁን ምግብ ስንት ሰዓት ላይ እንደሚበሉ መጠየቅን እና መናገርን ችለዋል። ለጄን ምላሽ በመስጠት እና ምግብ ስንት ሰዓት ላይ እንደምትበላ በመጠየቅ ልምምድ ያድርጉ።

*When do you have breakfast?*
*When do you have dinner?*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ጠቅላላውን ውይይት ደግመው ያዳምጡና መልስዎን ያመሳክሩ።

***Jane***
*Hi Chris, when do you have breakfast?*

***Chris***
*I never have breakfast.*

***Jane***
*When do you have dinner?*

***Chris***
*I have dinner at eight forty five.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! አሁን የተለያዩ ምግቦችን ስንት ሰዓት ላይ እንደሚበሉ ሰዎችን በእንግሊዝኛ መጠየቅ ችለዋል። የተማሩትን መለማመድን ያስታውሱ። ጓደኛ ይፈልጉና የተለያዩ ምግቦችን ስንት ሰዓት ላይ እንደምትበሉ በእንግሊዝኛ በመጠያያቅ ልምምድ ያድርጉ። ለተጨማሪ Essential English Conversation ዝግጅቶች በቀጣይ ክፍላችን ይጠብቁን። Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018